ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

# የጨዋታውን አሰላለፍ እንቀይር

በአገራችን በአሁኑ ጊዜ እየተካሄደ ያለው ተግባር የዕብደት ነው ቢባል የተጋነነ አይደለም፡፡ ለነገሩ አሠራሩ አዲስ አይደለም - ወደፊት ለማሰር ወይም “ለመምታት” የታሰበ አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሲኖር ሕግ ይወጣል ከዚያም ሕግን ከለላ አድርጎ የማሰር፣ የማዋከብ፣ የማሰቃየት፣ ወዘተ ተግባራት ይከተላሉ፡፡ ህወሃት/ኢህአዴግ ድሮ ጫካ የነበረ ጊዜ ሲከተለው የነበረ አሠራር ይኸው ነበር፤ አሁንም “በነጻ አውጪ ግንባር” ስም ለ20 ዓመታት የመንግሥት ሥልጣንን ይዞም እየተከተለ ያለው አሠራር ይኸው ነው፤ ወደፊትም ይቀጥልበታል፡፡ አሁን እየተደረገ ያለውን ትንሽ ለየት የሚያደርገው ህወሃት/ኢህአዴግ ወደፊት ልፈራ እችላለሁ ብሎ “ሕግ” ማውጣቱና ከዚያም “አንዴ ሕግ ካወጣሁ አይቀር ለምን አልፈራም” ብሎ በራሱ ላይ ሽብር ነዝቶ ውብሸት ታዬን፣ ርዕዮት ዓለሙን፣ በቀለ ገርባን፣ ኦልባና ሌሊሳን፣ ደበበ እሸቱን፣ እስክንድር ነጋን፣ አንዱአለም አራጌን፣ ወዘተ እንዲሁም ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞችን “በአሸባሪነት” ማሰሩ ነው፡፡ “ለከርሞ የሚያብድ ዘንድሮ ልብሱን ከፍ፣ ከፍ ያደርጋል” ይሏል ይኸው ነው፡፡

በተለይ በቅርቡ በሰሜን የአፍሪካ አገራት የተካሄደው ለውጥ የህወሃት/ኢህአዴግን ጡንቻ ክፉኛ አላልቶታል፡፡ የጋራ ንቅናቄያችን ከውስጥም ሆነ ከውጪ ባለው መረጃ መሠረት እንዲሁም በቅርቡ ይፋ የሆኑት የሹልክዓምድ[1] (WikiLeaks) እውነታዎች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ በአገዛዙ ውስጥ ፍርሃት ነግሷል፤ ተጽዕኖውም እያየለ መጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ በተቃዋሚ ስም ከተፈረጀው የአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ የሚመጣ ትችት ብቻ ሳይሆን ራሱ ህወሃት/ኢህአዴግየሚያውቀው እንደሆነ በተለያየ ጊዜየሚያፈተልኩትመረጃዎችማስረጃ ናቸው፡፡

ላለፉት ሃያ ዓመታት ህወሃት/ኢህአዴግ ያለማቋረጥ ጋዜጠኞችን፣ የፖለቲካ መሪዎችን፣ መምህራንን፣ ለውጥ ፈላጊዎችን፣ ተማሪዎችን፣ ወዘተ ሲያስር ቆይቷል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ በተለይ ምዕራባውያንን ለማሳመን ሕግን ሽፋን ማድረጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ምዕራባውያንን ጠንቅቀቀው አውቀውበታል፡፡ **ካሰረ በኋላ የመክሰሻ “ወንጀል” እንደሚፈልግ፣ ቦምብ ራሱ እያፈነዳ ንጹሕ ኢትዮጵያውያንን እንደሚከስ፣ ወዘተ የአደባባይ ምስጢር ሆኗል፡፡** ነገር ግን የህወሃት/ኢህአዴግ መሪዎች በፍርሃት ተሸብበው የሚባንኑ በመሆናቸው ከእነርሱ ወጣ ያለ አስተሳሰብ አስበዋል ያሏቸውን ሁሉ ከማሰር፣ ሞራላቸውን ለመስበር ከመሞከር፣ ወኔያቸውን ከማገት፣ ወዘተ ቦዝነው አያውቁም፡፡ ኢትዮጵያ የጀግና መካን አይደለችምና መቼም ቢሆን አይሳካላቸውም፡፡ ሆኖ ግን ይህ አሠራራቸው አንድ የተቀናጀና የተባበረ ኃይል ብቅ እንዳይል በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ሲያግት ቆይቷል፡፡

## 1. በ“ከፋፍለህ እሰር” ስልት የኢትዮጵያውያንን ልዩነትን በማስፋት፤

ታዋቂ ሰዎች በሚታሰሩበት በርካታ ኢትዮጵያውያን በመሰባበሰብ ተቃውሟቸውን ያሰማሉ፤ እንዲፈቱም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ዓይነት ኢትዮጵያዊ ከሁሉም ብሔር በአንድ ድምጽ ወጥቶ ሳይሆን የሚታገለው በቁጥር ውሱን የሆኑ ብቻ ናቸው፡፡ ህወሃት ግን በዚህ የተካነ ስለሆነ የሁልጊዜ የጥቃት ዒላማዎቹ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ በማነጣጠር አፈናውን፣ እስሩን፣ ግድያውን ይቀጥላል፡፡ ይህ ሲሆን የሚቃወመው ኃይል በአብዛኛው ኦሮሞዎች ብቻ

---

[1] ዲባቶ መስፍን አረጋ የቃሉ ተርጓሚ ናቸው፡፡

ይሆናሉ፡፡ ከኦሮሞ ሕዝብም ክርስቲያኑን እና እስላሙን በመከፋፈል ህወሃት ተግባሩን ሲፈጽም የተቃዋሚውም ኃይል እየተከፋፈለ ስብጥሩም እየተመናመነ ይሄዳል፡፡ ከዚህ አልፎ ሰለባዎቹ በኢትዮጵያ በጣም አናሳ ከሆኑት ብሔሮች እንደ አፋር፣ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ኦጋዴን አካባቢዎች እየሆነ ሲሄድ የተቃዋሚው ኃይል ከማነሱ የተነሳ ድርጊቱ እየተፈጸመ መሆኑን እስከ መርሳት ይደረሳል፡፡ በመሆኑም የህወሃት/ኢህአዴግ “ከፋፍለህ እሰረው” ዓላማ እየተሳካ የእኛም የተባበረ የተቃውሞ ኃይል እየተዳከመ ይሄዳል፡፡

## 2. **በማሰርም ሆነ በመፍታት ተጠቃሚው ህወሃት/ኢህአዴግ መሆኑ፤**

ህወሃት ሲያስር እኛ ስናስፈታ፤ ሲያስር - ስናስፈታ . . . በማያልቅ ጨዋታ ውስጥ እንገኛለን፡፡ ሲያስር ኃይላችን ይጠናከራል፤ የእርስበርስ ተቃውሟችን ይቀንሳል፤ ትብብራችን ይጎለብታል፤ ፍቅራችን ይጎመራል፤ . . . ሁኔታው አቅጣጫውን እየቀየረ ሲመጣ እንዲሁም ሌላ የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸም ሲፈልግ ህወሃት ታሳሪዎቹን ይለቃል፡፡ እኛም እንተነፍሳለን፤ ስንተነፍስ እንላላለን፤ ትብብራችንና ኃይላችን ይረግባል፡፡ ይህ በተለያየ ጊዜ የተከሰተ እውነታ ነው - የቅንጅት አመራሮች፣ ቴዲ አፍሮ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ወዘተ በታሰሩና ጊዜና ከተፈቱ በኋላ የሆነውን ቆም ብሎ ማጤኑ ይበጃል፡፡

## **የጨዋታውን አሰላለፍ እንዴት እንቀይር?**

ህወሃትም ሆነ ሌላው ወገን ሁሉ ያልተረዳው ነገር ከበስተጀርባ የሚደረግ በርካታ ሥራ መኖሩን ነው፡፡ ይህም ሥራ ይፋ ሆኖ እንቅስቃሴው በሚቀጥልበት ጊዜ ጨዋታው በተመሳሳይ ሁኔታ ፈጽሞ አይቀጥልም፡፡ **ስለሆነም ሥራችን ህወሃት/ኢህአዴግ በሚሰጠን የቤት ሥራ በመንቀሳቀስ እነርሱ ሲያስሩ እኛ ስናስፈታ የምንቀጥልበት ሁኔታ ሳይሆን የሁላችንም የትኩረት አቅጣጫ ኢትዮጵያን “ከነጻ አውጪው” ነጻ ማውጣት መሆን አለበት፡፡** ይህ ደግሞ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ የተጠናከረና የሰከነ አስተሳሰብ ይጠይቃል፡፡ **ድፍረታችን፣ ጀግንነታችንና ወኔያችን አካላዊ ብቻ ሳይሆን ሞራላዊ መሆን አለብን፡፡** በሁሉም መስክ ከፍተኛውን የሞራል ልዕልና መያዝ አለብን፡፡

የጋራ ንቅናቄያችን አመራር የሆኑት አቶ ፈቃደ ሰማኔ በአሁኑ ወቅት ያለውን ሁኔታ ሲያስረዱ “**ህወሃት እኮ ኢትዮጵያን እንደ ቄራ ነው ያደረጋት፡፡ የቄራው ባለቤት በፈለገው ጊዜ እየመጣ የፈለገውን ከብት እያወጣ በተለይም ደግሞ አመጸኛውን እየነጠለ በማውጣት እንደሚያርድ ህወሃትም እንዲሁ ነው እያደረገ ያለው፡፡ አራጁ ይህንን ሲያደርግ ሌሎቹን ከብቶች ጸጥ እንዲሉ በማድረግ የበረቱን (የቄራውን) ሰላም እጠብቃለሁ በማለት አስቦ ሲሆን ለተወሰነ ጊዜም ከብቶቹ ጸጥ ይላሉ፡፡ ግን አይቆይም ሌላ አመጸኛ ደግሞ በረቱን ያናጋዋል፡፡ አራጁም ሥራውን ይቀጥላል፡፡ ከብቶቹ ተባብረው በረቱን ጥሰው ካልወጡ ወይም አመጻቸውን አቁመው ጸጥ እስካላሉ ድረስ ድርጊቱ አይቆምም፡፡ የኢትዮጵያ ሁኔታም ይኸው ነው፤ ኢትዮጵያውያን ግን ጸጥ የማይሉበት ጊዜ እየመጣ ነው፤ እንዲያውም አሁን እየሆነ ነው ማለት ይቻላል**” ብለዋል፡፡

ወደኋላ ሄደን እንደ ቴዲ አፍሮ ዓይነት በሕዝብ ዘንድ የተወደደ ባለሙያ እናስብ፤ በአንድ የኪነት ውጤት በሁሉም ሰው ልብ ውስጥ መሥረጽ የቻለ ነበር፤ አሁን ግን ጸጥ ብሏል፡፡ ተመሳሳይ ነገር በቅንጅት አመራሮች ላይ ተፈጽሟል፤ አሁን ደግሞ በወ/ት ብርቱካን ላይ፡፡ ዓላማቸው ጸጥ ማሰኘት፤ መከፋፈል፤ ከአገር ማባረር፤ … ነው:: ይህን ተግባራቸውን ቀጥለውበታል እኛም የጨዋታውን ስልት ሳንቀይር መከተሉን ቀጥለንበታል፡፡ ከላይ አቶ ፈቃደ እንዳሉት በዚህ ሁኔታ የምንቀጥልበት ሁኔታ አይኖርም፤ **ኢትዮጵውያንም በተመሳሳይ የአጨዋወት ስልት የተለየ ውጤት መጠበቅ ማቆም አለብን፡፡**

የጨዋታውን አሰላለፍ ለመቀየርና ስኬታማ ተግባር ለመፈጸም ሁሉንም ተቃዋሚ ኃይላት በአንድ ማሰባሰብ ወይም አንድ ማድረግ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ አሠራር ካልሰራ እዚያ ላይ ሙጭጭ ማለቱ ውጤታማ አይሆንም፡፡ **ከዚያ ይልቅ ግን በሁሉም**

የኅብረተሰብ ክፍል ተቀባይነት ያላቸውን ጥቂት ቅን ኢትዮጵያውያንን ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ ወሳኝና ተግባራዊ ለሆነ ሥራ በማሰማራት ኢትዮጵያን አሁን ካለው የህወሃት/ኢህአዴግ “የነጻ አውጪ ግምባር” አገዛዝና ወደፊት ሊመሰረት ከሚችል ሌላ አምባገነናዊ አገዛዝ መንጭቆ ማውጣት ነው፡፡ ለዚህ ተግባራዊነትም የግድ የቱኒሲያን ወይም የግብጽን ወይም የሊቢያን ወይም የየመንን ወዘተ መንገድ መከተል አያስፈልግም፡፡ የጥቁር ሕዝብ መመኪያ የሆነችው ኢትዮጵያ ሁልጊዜ የራሷ መንገድ ነው ያላት - ይህም አንዱና ብቸኛው የኢትዮጵያ መንገድ ነው!! ለዚህም የሚያስፈልገው “ከዘረኝነት ይልቅ ሰብዓዊነትን” የሚያስቀድም የመንፈስ ልዕልና እና አሻግሮ የሚያይ ራዕይ ነው፡፡

ወገኖቻችን የሆኑት እስክንድር ነጋ፣ አንዱአለም አራጌ፣ ውብሸት ታዬ፣ ርዕዮት ዓለሙ፣ በቀለ ገርባ፣ ኦልባና ሌሊሳ፣ ደበበ እሸቱ፣ ወዘተ ታላላቅ የፍትሕ አርበኞች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ሌሎች ያልተገጠመላቸው፣ ያልተጮኸላቸው፣ ስማቸው እስካሁን ያልተጠቀሰ፣ በርካታ ጀግኖች አሏት፡፡ ኢትዮጵያ የአካልም ሆነ የመንፈስ ጀግና ድሃ ሆና አታውቅም፡፡ እነዚህ ሁሉ ከተለያየ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የህይወት መስመር፣ ወዘተ የመጡ ናቸው፡፡ እነዚህም ሆነ መላው ኢትዮጵያዊ ነጻ ሳይሆን አንዳችንም በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ነጻ መሆን አንችልም፡፡

ስለሆነም የአጨዋወት ስልታችንን በተለይም የሰልፍ ተቃውሟችን ላይ አጥብቀን ልናስብበት ይገባናል፡፡ እጅግ ታዋቂ ለሆኑ ሰዎች ብቻ መጮሃችንን በጥንቃቄ ልናጤነው ያስፈልጋል፡፡ ከእንግዲህ ሰልፋችንም ሆነ ጩኸታችን ለራሳችን እና ለመላው የአገራችን ሕዝብ መሆን ይገባዋል፡፡ የቤት ሥራ እየተሰጠን የምናደርገው ትግል ሊበቃን ይገባል፡፡ ባለፉት ህወሃት/ኢህአዴግ ሲያስር እኛም እየጮህን ስናስፈታ አንዳንዶችም ሲሞቱ ሌሎቹም እስካሁን እንደታሰሩ ወይም የደረሱበት ሳይታወቅ ሃያ ዓመታት አለፉን፡፡ ፐ/ር አስራት ወ/የስ፣ ዶ/ር ታየ ወ/ሰማያት፣ ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያም፣ ወ/ት ሌሊሴ ወዳጆ፣ አቶ በሽር መክታል፣ አቶ በቀለ ጅራታ፣ አቶ ጁማ ሩፋዒ፣ አቶ ሳበል አልዳክሂት፣ አቶ የማነ ገ/አብ፣ ወ/ት አበራሽ በርታ፣ ሻለቃ አዱኛ፣ ወዘተ ስንቱን ጽፈን እንችለዋለን? ይበቃናል የጨዋታውን አሰላለፍ እንቀይር!

ከላይ እንደጠቀስነው በፊት ለፊት የማይታይ ከበስተጀርባ የሚካሄድ በርካታ ሥራ አለ፡፡ይህም ሥራ እነዚህ ቆጥረን የማንዘልቃቸውን ጀግኖቻችን ከእስር ማስፈታት ብቻ ሳይሆን አገራችንን ከዘረኝነትና ከአምባገነንነት ማስፈታት ነው፡፡ ጊዜው የሚሆነውም በዋሽንግተን ሰዓት ወይም በለንደን ሰዓት ወይም በአውሮጳ ሰዓት ሳይሆን ከፈጣሪ የጊዜ ቀመር ጋር በተዋሃደው ብቸኛው በኢትዮጵያ ሰዓት ነው፡፡ ይህ እስከሚሆን ደግሞ አናርፍም፤ አንታክትም፤ ዝምም አንልም፡፡

ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ፈጣሪ ሁላችንንም ያነሳሳን፤ ድፍረትን፣ ሃቀኝነትንና ቅንነትን ይስጠን፡፡ ለታሰሩት ወገኖቻችን እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው የመንፈስ ብርታትና ጽናት ይስጣቸው፡፡ በዘረኝነት፣ በጥላቻ፣ በፍቅረ ንዋይ፣ በእብሪት ለታወሩት መንፈሳዊ ዓይናቸውን ያብራላቸው፡፡ብቸኛዋን አገራችንን፣ ክብራችንን፣ መመኪያችንን ኢትዮጵያን ለማዳን የተነሳነውን ሁሉ ደግሞ በአገራችን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ **“በሕግ አምላክ!”©** እስኪሰፍን በጽናት እንቁም!!

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

